# ዓባይና የስኬት ጉዞው

**እንዳልካቸው ለማ 03/03/14**

“…ኢትዮጵያ ፈጣን ልማት ማረጋገጥ ካለባት የተፈጥሮ ሐብቷን በአግባቡ መጠቀምና መንከባከብ አለባት። የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት የራስዋን ፍላጎት ከማሟላት አልፋ ሱዳንና ግብፅን ጨምሮ ለጎረቤት ሀገሮች በመሸጥ የውጭ ምንዛሪ በማግኘት በአፍሪካ ቀንድ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲኖር ማድረግ አለባት።…”ይላል - የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የሀገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ። ይህ ሰነድ ታትሞ በይፋ ወደ ሕዝብ ከደረሰ እነሆ 11 ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡

ቀድሞ የተነገረ ትንቢት ይመስላል፡፡ ትልሙ ግን ወደ ተግባር መሸጋገር ከጀመረ ዛሬ ሦስት ዓመታትን ሊደፍን ቀናት ቢቀሩት ነው፡፡ በሰነዱ ላይ እንደሰፈረው የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት የራስን ፍላጎት አሟልቶ ለጎረቤት ሀገሮች የመሸጥ ውጥን ወደ ተግባር የመለወጥ እንቅስቃሴ ተጀምሮ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ተግባራዊ እንቅስቃሴ “ትንቢት ይቀድም ለነገር” የሚለውን ቅዱሣዊ ቃል ያስታውሰናል። እርግጥ ነው ትናንት ላይ ሆኖ ነገን በሚገባ ተመልክቷል። የትናንት ራዕያዊ እሳቤዎቹን ትክክለኛነትንም የዛሬው ተግባሩ አረጋግጧል።

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሁሌም በሚያናፍሱት የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ በእፍረት ላይ እፍረት የሚከናነቡት ጨለምተኞች ከሚከለሉበት ሥርቻ ተጠራርተው የተሰባሰቡ “ወፍ ዘራሽ” ፖለቲከኞች ማንነትን ገላልጦ እርቃናቸውን የእውነት ፀሐይ በአደባባይ እንዲሞቀው አድርጓል።

በዋነኛነት ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብሩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን ካካተተበት ከዚህ ሰነድ 158 ገፆቹ መካከል በአንዱ ላይ እንዲህ የሚል ሰፍሮ ይነበባል፡፡ ይህ ጉዳይ የትናንቱ እቅድ በዛሬው ክንውን ውስጥ ተጨባጭ እውነታ ተላብሶ ምን እየተከናወነ እንዳለ በግልጽ የሚያመላክት ነው።

ሆኖም ይህን መሰሎቹን የሰነዱን ትናንታዊ ትልም ባለፉት 11 ዓመታት ውስጥ ቀንብቦ መመልከት አይቻልም። ገዥው ፓርቲ የሕዝቦችን የዘመናት ጥያቄ አንግቦ ይታገል ስለነበር በዚያን ወቅት የተወጠነውን ይህንኑ ሰነድ ሀገራዊ አመለካከት አንፀባራቂ ነው ብሎ ማለፉ ያግባባል – የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂን።

ከዚህ ፖሊሲና ስትራቴጂ ጋር ፊፅሞ የማይተዋወቁና ሀገራዊ የምርጫ ወሬ በተሰማ ማግሥት የሚቧደኑ ስብስቦች በየሚዲያው የሚያናፍሱት የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ግን ሁሌም ማንነታቸውን እንዳጋለጣቸው ነው።

ሰነዱ ኢትዮጵያ እና ግብፅ በዓባይ ጉዳይ ላይ ሊኖራቸው ስለሚገባ በፍትሃዊነትና እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረተ ጥቅሞችን የማጣጣም መርህን ይዟል፤ ጽንፈኞቹ ግና ይህን ሊያዩት አይፈቅዱም፡፡ የደፈና ጥላቻ ስብስቦች ናቸውና በየጊዜው ከሚለፍፉትና እርስ በርሳቸው ከሚጋጩ ዲስኩሮቻቸው መላቀቅ አልቻሉም፡፡ በጥላቻ ላይ የሚያጠነጥኑት መግለጫዎቻቸውም ቢሆኑ "አጀብ" ከሚያሰኝ ውሸት በቀር ጠብ የሚል ቁም ነገር የላቸውም።

ሲያሻቸው ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይልን በማመንጨት የራስዋን ፍላጎት አሟልታ ለጎረቤቶቿ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን ማግኘት ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ሀገራት መካከል ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር መፍጠር የሚለው የእኛ ፕሮግራም ነበር ሲሉ ድርቅ ይላሉ፡፡ ዳሩ ምን ያደርጋል/ "አጀንዳው የእኛ ነበር፤ ግን ተነጠቅን።" ሲሉም ባፈጠጠና ባገጠጠ ቅጥፈታቸው ይወሸክታሉ፡፡

"ለመሆኑ የትኛው አጀንዳ?" ተብለው ጠበቅ ተደርገው ቢጠየቁ ምላሽ እንደሚያጥራቸው አይጠራጠሩ፡፡ ግን ደግሞ ዓይኖቻቸውን በጨው ታጥበው በፈጣጣ "የዓባይን ነዋ!" ብለው ቢሏችሁ ልትገረሙ አይገባም።

እርግጥም እነ "አጅሬ" ተነጠቅን የሚሉት የዓባይ ወንዝን በመገደብ እየተገነባ የሚገኘውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን የራሳቸው አጀንዳ አድርጎ ለመያዝ ማሰቡ ያስተዛዝብ ካልሆነ በቀር የሚያስገኘው ፖለቲካዊ ትርፍ የለም፡፡ አጀንዳው የማን እንደሆነ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጥረቱ ውጤት ጭምር።

በወርሃ ህዳር 1995 ዓ.ም ይፋ የሆነው የውጭ ጉዳይና የሀገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ "...ኢትዮጵያ በዓባይ ተፋሰስ ላይ ፈጣን ዕድገትን ለማሳካት የሚያስችል ተግባር ካልከወነች የልማት ሥራዎቿ ሊፈፀሙ አይችሉም። ይህንንም የታችኛዎቹን የተፋሰስ ሀገሮች መሠረታዊ ጥቅም በማይነካ፣ ጥቅሞችን በሚያጣጣም አኳኋን ማድረግ ይቻላል፣ ይገባልም።..." በማለት መንግሥት የዓባይን ወንዝ አጠቃቀም አስመልክቶ አቋሙን ይፋ አድርጓል።

ሁሌም የኢትዮጵያን ሕዝብ በውሸት ወሬ ለማደናገር ሲጥሩ የሚከርሙት ተቃዋሚዎች መቼ የነደፉትን የዓባይ አጀንዳ ነው የተነጠቁት? ከመቼ ወዲህስ ስላልፈጠረባቸው ሀገራዊ ዕድገት ማሰብ ጀመሩ? ዓባይ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያለው ትልቅ ፕሮጀክት መሆኑንነ የግዳቸውን በተረዱ ጊዜ ዓይኖቻቸውን በጨው ታጥበው "አጀንዳው የእኛ ነበር፣ ተነጠቅን" የሚል አሳፋሪ ስብቀትን መረጡ፡፡

እውነታው ግን ይህ አይደለም። እነዚህ ኃይሎች ከአደናቃፊ ተግባራቸው ተላቅቀው እንዲህ ዓይነቱን በጎ ነገር የሚያስቡበት አዕምሮም ይሁን ባህሪያዊ ተፈጥሮ የላቸውም።

ታዲያ ይህን እርቃኑን የቀረ የውሸት ድሪቶ እዚህ ላይ እንግታውና ባለፉት ሦስት ዓመታት ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ ከዋንኞቹ የግንባታ ሥራዎች በተጓዳኝ የተከናወኑ ሌሎች ተያያዥ ተግባራትን እንዳስስ።

በአሁኑ ወቅት የግድቡ ዐበይት ሥራዎች በሦስቱም ፈረቃዎች ተጠናክረው መቀጠላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዲፕሎማሲውም መስክ ተጨባጭ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የግብጽን የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያቀፈ የልዑካን ቡድን ከዓባይ ውኃ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ስላለው ተጨባጭ እውነታ እንዲገነዘብ መደረጉ አንዱ ነው፡፡

መንግሥት ራሱ በነደፈው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እየተመራ ባከናወናቸው በርካታ ጥረቶች ማቢያ በተጎናፀፈው ታላቅ የዲፕሎማሲ ድል ምክንያት የመጣ ውጤት ነው፡፡ ከዚህ ውጤት በይበልጥ መረዳት የሚቻለው ሙሉ በሙሉ ባይባልም የግብፅን ሕዝብ የ"ድሮ" እና "ዘንድሮ" የአመለካከት ልዩነት መፍጠር መቻሉ ነው፡፡

ኢትዮጵያ እና ግብፅ ዘመናትን የተሻገረ ታሪካዊ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርና ቁርኝት ያላቸው ሀገራት ናቸው፡፡ ይሁንና በዓባይ ወንዝ ምክንያት ግንኙነታቸው የሚጠበቀውን ያህል ተጠናክሮ አልቀጠለም፡፡

ለዚህም ግብጽን በየተራ ሲመሯት የነበሩት መንግሥታት የዓባይን ወንዝ የውስጣቸውን የፖለቲካ ትኩሳት ማብረጃ መሣሪያ አድርገው ሲጠቀሙበት መቆየታቸው በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡ መንግሥታቱ ኢትዮጵያ የዓባይ ውኃን መጠቀም ከጀመረች ሀገራቸው ለከፍተኛ አደጋ እንደምትጋለጥ በማስመሰል ሕዝቡን ሲያደናግሩት ኖረዋል፡፡

አንዳንዶቹም ሀገራቸውና ሱዳን ብቻ እ.ኤ.አ በ1959 የተፈራረሙትን የቅኝ ገዥዎች ውል በመጥቀስ፣ ኢትዮጵያ ከውኃው አንድም ጠብታ መጠቀም እንደሌለባት ለሕዝባቸው ሲገልጹ ኖረዋል፡፡ ለዓባይ ወንዝ በምንጭነት ከ85 በመቶ የማያንስ ውኃ የምታበረክተው ኢትዮጵያ ኢ-ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የበይ ተመልካች እንድትሆን ያልተከናወነ ድብቅና ግልጽ ሴራ አልነበረም፡፡ በዚህም በሕዝባቸው ውስጥ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን መፍጠር ችለዋል፡፡

በተለይ በሆስኒ ሙባረክ የአገዛዝ ዘመን ወቅት፣ ሕዝቡ ውስጣዊ ችግሮቹን እንዳይመለከት የዓባይ ጉዳይ በዋነኛ "የአደንዛዥ እፅነት" ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ሥርዓቱ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ

ከመሆኑም በላይ፣ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት እንዲቀጭጭ ብሎም የሕዝቡ ተጠቃሚነትንም ያላረጋገጠ ነበር፡፡

በዚህም ሣቢያ በመላው ግብጽ ከፍተኛ ሥራ አጥነት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ታዲያ ሕዝቡ ውስጣዊ ችግሩን እንዳይመለከት አገዛዙ "ኢትዮጵያ ዓባይን ልትጠቀም ነው፤ ውኃችንም ሊቀንስ ይችላል" የሚል ማደናገሪያ በመፍጠር ወንዙን የፈላጭ ቆራጭ ሥርዓቱ መደገፊያ ምሶሶ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ ሕዝቡም ላለፉት 30 ዓመታት ይህንን ደግፎ እንዲቆምና ኢትዮጵያንም በመጥፎ ዓይን እንዲመለከታት የሚያደርግ ስሜት ሲፈጥር ኖሯል – እውነታው ሲገለፅ የሥርዓቱ ህልውና "ሲያልቅ መጨረሻው አያምር" እንዲሉት ዓይነት ሆነ፡፡

በዚህም ሆነ በዚያ፤ የግብጽ ሕዝብ በገዥዎቹ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ የተዛባ አመለካከት እንዲኖረው ከመደረጉም በላይ፣ ዐረባዊ እንጂ አፍሪካዊ ማንነቱም እንዲጠፋ ጥረት ተደርጓል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ የግብጽን ሕዝብ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክለው የልዑካን ቡድን ወደ አዲስ አበባ መምጣት ምን ጠቀሜታ ነበረው ብሎ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

የልዑካን ቡድኑ በቀደምት ገዥዎቹ የዓባይ ጉዳይ አስመልክተው ሲነግሩት የነበረው አፈ-ታሪክ ትክክለኛ አለመሆኑን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተገንዝቧል ማለት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በዓባይ ወንዝ ላይ ጥቅሞችን ለማጣጣም የሚሰሩ እንጂ፣ የግብጽ ሕዝብ ጠላት አለመሆናቸውን እዚሁ መጥቶ ካየው ነገር ተረድቷል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር በጋራ ተጠቃሚነት መርህ እጅ ለእጅ ተያይዛ የማደግና በሠላም አብሮ የመኖር ፍላጎት እንዳላት የልዑካን ቡድኑ በወቅቱ እውነታውን ተረድቷል ተብሎም ይገመታል፤ ልማታዊ መንግሥታችንም ሀገሩን ጠቅሞ ጎረቤቶቹንም የሚጠቅም ፖሊሲ እንዳለውና ወደ ተግባር እንደገባም ግልጽ ሆኖለታል - "አውቆ የተኛ …" ካልተባለ በቀር፡፡ ፡፡

ታዲያ ለሠላም የተዘረጉት የሀገራችንን እጆች ለመጨበጥና ተጠቅሞ የመጠቀም መርህን የጋራ ለማድረግ በወቅቱ ወደ መዲናችን ያቀናው ልዑኩ ከመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተና መግባባት የሰፈነበት ውይይት አካሂዷል፡፡

ለማስታወስ ያህል በዚያን ውይይት ወቅት የተነሳው ጉዳይ ግብጽ ምርጫ እስከምታካሂድ ድረስ ስድስቱ የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የተስማሙበትን ሰነድ መንግሥታችን ለፓርላማ አቅርቦ የሚያፀድቅበትን ጊዜ እንዲያራዝም የሚጠይቅ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትም በጊዜው ይህንኑ ጥያቄ ተቀብሎታል፡፡ ይህ ጥያቄ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ተቀባይነት ያገኘው በሁለት ምክንያቶች ነበር፡፡ አንደኛው ከመንግሥታችን ሕዝባዊ ባህሪ፤ ሁለተኛው ደግሞ ሀገሪቱ ከምታራምደው ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ ነው፡፡

ምንም እንኳ አብዛኛው የግብጽ ሕዝብ በቀደምት ገዥዎቹ አማካይነት ሀገራችንንና ጥቁር ሕዝቦችን አስመልክቶ እንዲቀበላቸው የተደረጉ የተዛቡና ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን የያዘ ቢሆንም፤ እንደ ሕዝብ ወዳጅ እንጂ ጠላት አይደለም፡፡ መንግሥትም በባህሪው ሕዝባዊ ወገንተኝነት የተላበሰ በመሆኑ የየትኛውም ሀገር ሕዝብ በመተማመንና በወዳጅነት መንፈስ የሚመለከት ነው፡፡

እናም ያኔ የኢትዮጵያ መንግሥት የልዑኩን ጥያቄ መቀበሉ ወክሎ ለላከው የግብጽ ሕዝብ ያለውን ከበሬታ የሚያመላክት ነው፡፡ ሀገራችን ከዚህ በፊት የግብጽ መሪዎች መጥፎ ተግባር ፈፅመዋል በሚል በሕዝቦች ሥቃይና መከራ የምትደሰት አይደለችም - የችግራቸው ተካፋይና የመፍትሄው አካል እንጂ፡፡ ይህ የኢትዮጵያ መንግሥት ባህሪያዊ ማንነት ትናንት የነበረ፣ ዛሬም ያለና ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡ ለልዑኩ የተሰጠው ምላሽም ከዚህ ነባራዊ እውነታ የመነጨ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የልዑኩ ጥያቄ በመንግሥት በኩል ተቀባይነት ያገኘበት ሌላኛው ምክንያት ጉዳዩ ሀገራችን ከምትከተለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋር የማይጋጭ በመሆኑ ጭምር ነበር፡፡ ሰነዱ ግብጽን አስመልክቶ «…የዓባይ ጉዳይ ጥቅሞችን በማጣጣም መርህ በሠላምና በድርድር የልማት እንቅስቃሴያችንን በማይጎዳ መልኩ እንዲፈታ፣ በዚህ ዙሪያ የሚነሱ ጉዳዮች በቂ ጊዜ በሚሰጥ አኳኋን እንዲታዩ ማድረግ ይሆናል፡፡…” ይላልና፡፡

ኢትዮጵያ የምትከተለው አካሄድ በተብራራ መልኩ ተቀምጧል፡፡ ይህም መንግሥት በዓባይ ጉዳይ ፍትሃዊ የሆነ የሁለትዮሽ ጉዳይ ተጠቃሚነትን በሚያስብበት ወቅት፣ ሠላማዊ ተግባሩን በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ውይይት እንዲሁም በችኮላ ሳይሆን ጊዜ በሚሰጥ ሁኔታ እንደሚያከናውን የሚያሳይ ጭምር ነው፡፡ የጋራ ተጠቃሚነትንና ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስጠብቀው የመንግሥት የይሁንታ ምላሽም ከዚህ አንጻር እንደሚታይ ማንም ሊገነዘበው ይችላል፡፡

በዚያን ወቅት ታዲያ አንዳንድ በውጭ የሚኖሩና ሁሌም ቢሆን ከጦርነት ውጭ ልማታዊ ጉዳይ የማይታያቸው ተቃዋሚዎች እና የውጭ ሚዲያዎች በድረ-ገፆቻቸው "ፓል ቶክ" እና ባገኟቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የሚያናፍሱት ውዥንብር በጣሙን የሚያስገርሙ ነበሩ፡፡ እስቲ ወደ ኋላ መለስ ብለን እናስታውስ፣ እንዲህ የሚልም ይገኝበት ነበር፡፡

ይኸውም "አል-መስሪ" የተባለ የግብጽ ጋዜጣ በስህተት ይሁን በማወቅ የኢትዮጵያ መንግሥት ታላቁ የህዳሴ ግድብ የግብፅን የውኃ ድርሻ የሚጎዳ ከሆነ ፕላኑን እንደሚቀይርና እንደገና እንደሚያጠናው ገልጿል የሚል ትክክለኛ ያልሆነ ዘገባ ነበር፡፡

እርግጥ በሚዲያ ሥራ ውስጥ መሳሳት ሊያጋጥም ይችላል - በእውነትም ጋዜጣው ተሳስቶ ከሆነ፡፡ ነገር ግን ጋዜጣው በቀደምት ገዥዎቹ ሲነገረው የነበረው አስተያየት በውስጡ ሰርፆ የሚያስበውም የሚዘግበውም በዚሁ ስሌት ተቀኝቶ ከሆነ ግን ዛሬ ላይ ተቁሞ ሲታይ አሁንም ያስተዛዝባል፡፡

በውጭ የሚኖሩና የቀድሞው ሥርዓት ርዝራዥ የሆኑ "ተቃዋሚዎች ነን" ባዮችም ሆኑ ሀገር ውስጥ "በሠላማዊ መንገድ እንታገላለን" የሚሉት የውስጥ የአመጽ አባቶች የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታን ሲቃወሙ የኖሩ ናቸው፡፡ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሀገር አስተሳሰብ ያላቸው ተቃዋሚዎች በዚህ ዙሪያ ያኔ ብዙ ብለዋል፣ ልሣኖቻቸውም ኢትዮጵያን ለማፈራረስ በተነሱ ኃይሎች ጥሪዎች ተሞልተው - ዳሩ ምን ያደርጋል ሰሚ አጡ እንጂ፡፡

ኸረ ለመሆኑ ተቃዋሚዎቹ "ኢትዮጵያውያን አይደሉም እንዴ?" ያስብላል፡፡ ዘመቻ እና ቅስቀሳዎቻቸው ጉድ የሚያሰኙ ነበር፡፡ ሀገራችንን በማፍረስ ሥራ ላይ በተጠመዱ ልሣኖቻቸው አማካይነት "ለግድቡ ገንዘብ እንዳታዋጡ፣ ቦንድ አትግዙ" እንዳላሉ ሁሉ

የያኔውን የአልመስሪ ጋዜጣን የተዛባ ዘገባ ሳያረጋግጡ አንጠልጥለው በማጯጯህ ተሽቀዳድመው ለግድቡ መገንባት ተቆርቋሪ በመምሰል የሚያናፍሱት አሉባልታ እውነተኛ የቀበሮ ባህታዊነታቸውን በገሃድ የሚያሳይ ነበር፡፡

ትናንት ሲያራምዱት የነበረው የ"ገንዘብ አታዋጡ፣ ቦንድ አትግዙ" ቅስቀሳ፣ ሕዝቡ ከድህነት ለመውጣትና ታሪኩን ለመቀየር ባለው ፅኑ ፍላጎት ሣቢያ አከርካሪው በመመታቱ ህልማቸው መና የቀረው አንዳንድ ተቋዎሚዎች፣ ተገልብጠው የግድቡ ጠበቃ መስለው ለመታየት "የኢትዮጵያ መንግሥት ከግብጽ ልዑካን ጋር ያደረገው ድርድር የሀገሪቱን ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ ነው፡፡ ኤርትራን ለመውረር እየፈለገ ስለሆነ የግብጽን ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ለማርገብ ነው" የሚል የፈጠራ ድርሰት አስኮምኩመውናል -ያኔ፡፡ መቼም የተቃዋሚዎቹ እንዲህ ዓይነቱ ግብ የለሽና በጭፍን ጥላቻ ላይ የተመሰረተ እስስታዊ ባህሪን የተላበሰ ልቦለዳዊ ትረካ መልሶ ራሳቸውን ከማጋለጥ ውጭ ምንን እርባና አላስገኘም፡፡

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት በወቅቱ ከግብጽ ልዑክ ጋር የተወያየው ዋነኛው ጉዳይ ስድስቱ የላይኛው የዓባይ ተፋሰስ ሀገራት የተፈራረሙትን ስምምነት ለፓርላማው የሚያቀርብበትን ጊዜ እስከ ግብጽ መንግሥት ምሥረታ ድረስ ለማራዘም ነበር፡፡ ይህም በውጭ ፖሊሲያችን የሚደገፍና የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በምንም ዓይነት መልኩ አሳልፎ የሚሰጥ አልነበረም፣ አይደለምም፡፡ እንዲያውም በሁለትዮሽ የጋራ ተጠቃሚነት ከዚህ በፊት ያልነበረንን የልማት ትሩፋቶች የሚያቋድሰን ነው፡፡

የግድቡ ግንባታ በፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ በሚገኘው ምጣኔ ሀብታችን ሣቢያ፣ ግብርናው የመሪነት ሚናውን በሂደት ለኢንዱስትሪው ሲያስረክብ ለሚፈጠረው ከፍተኛ የኃይል ፍላጎት ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡

በተለይም የኤሌክትሪክ ኃይልን በመሸጥም የውጭ ምንዛሪ አቅማችን እንዲጎለብት ያደርጋል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ መንግሥት የነደፈው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን በማሳካት የሀገራችን ህዳሴ በጽኑ መሠረት ላይ ያኖራል፡፡ ታዲያ እነዚህ ተግባራት በምን ዓይነት ተቃውሞአዊ የሂሳብ ቀመር ነው የሀገራችን ጥቅም አሳልፈው የሚሰጡት?

መቼም ነገሩ "ሰይጣን ላመሉ ከመፅሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል" እንዲሉ ሆኖ እንጂ እነዚህ ተቃዋሚዎች በደፈናው ከማጥላላትና ከመተቸት ውጪ ስለ ሀገር ልማትና ዕድገት የሚያስቡ እንዳልሆኑ በግልፅ ያስገነዝባል፡፡ ለዚህም የማንነታቸው እውነተኛ መገለጫ የሆነውን የፀረ-ሕዝብነትና ፀረ-ልማትነት መለያ እንደ እባብ ቆዳ ገሽልጠው በመጣል፣ በማይታወቀው እነሱነታቸው ብቅ ብለው በአሉባልታ የበሬ ወለደ ማደናገሪያ የዚያን ሰሞነኛ ልቦለዳቸውን ብቻ መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ያኔ ለውይይት ወደ ሀገራችን የመጣው የግብጽ ልዑክ የዓባይን ውኃ የጋራ ጥቅምን መሠረት ባደረገ መልኩ በሠላማዊ መንገድ ለመጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ለመነጋገር ነበር ወደ ሀገራችን የዘለቀው፡፡ የሁለቱን ሀገራት ሕዝቦች በማቀራረብ ወንድማማችነትንና የእኩል ተጠቃሚነት መርህን በማንገብ ነበር የተንቀሳቀሰው፡፡

ያኔም ቢሆን ልዑኩ በሀገራችን ሚዲያዎች ጭምር "በቅኝ ግዛት ወቅት የተፈረሙት ውሎች ትክክል አልነበሩም" እያሉ ሲቃወሙ በግብፅ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ መልኩ ማድመጣችን ይህን ሀቅ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ከዚህ ውጭ የነገር አደራን በማስቀመጥ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን ለመውረር ስለፈለገ ለመነጋገር ነው የመጡት የሚል አንደምታ ያለውን አፈ-ታሪክ ፈጥሮ ማውራት፤ "ተቃዋሚ ነን" የሚሉትን ኃይሎች የዘቀጠ የአስተሳሰብ ደረጃን ከማረጋገጥ ውጪ ማደናገሪያው ውኃ የማይቋጥር ነው-ጭራሽ የሚያስተዛዝብ፡፡

ይኸውም በቅድሚያ ሀገራችን የምትከተለው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሠላም እንጂ የወረራ አለመሆኑን ባህር ማዶ ሆነው ቅዠታዊ የጦርነት ድቤ የሚመቱት እነዚህ ወገኖች ሊያውቁት ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት "የኤርትራው የትርምስ ቡድን እንዲወገድ እሰራለሁ" በማለት የገለፀው ለሠላም፣ ለልማትና ለዴሞክራሲ የሚተጉ ኤርትራዊያን ኃይሎችን በመደገፍ እንጂ በወረራ አይደለም፡፡ የአሥመራው አስተዳደር በሀገራችን ላይ ቀጥተኛ ወረራ እስካልፈፀመ ድረስ በምንም ዓይነት መንገድ ኤርትራን የመውረር ፍላጎትም ሆነ ተነሳሽነቱ የለውም፡፡ ለምን ቢባል መንግሥት ከጎረቤቶቹ ጋር በሠላም፣ በመከባበርና

ተያይዞ በማደግ ላይ የተመሠረተ ፖሊሲን የሚከተልና የማንንም ሀገር ሉዓላዊነትን የሚደግፍ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

ይህን "ኤርትራ ልትወረር ነው" የሚል የሐዘን እንጉርጉሮን ያዘለ አሉባልታን በድረ-ገጻቸው በ"ፔን ፓል" አማካይነት ስማቸውን እየቀያየሩ የሚፅፉት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ግሃድ ነው፡፡ የዚህ አባባል ባለቤቶች በሻዕቢያ ተቃውሞአዊ ስሌት የሚንቀሳቀሱ "ተቃዋሚ ነን" ባይ ሴረኛ ፖለቲከኞች ስለመሆናቸው ለማወቅ ብዙም እውቀት አይጠይቅም፡፡

እነዚህ ኃይሎች ሀገራቸውን በመካድ እንደ ውኃ ቀጂ በየማምንቱ አሥመራ ሲመላለሱ፣ በገዛ ሕዝባቸው ላይ ሲያሴሩና የሀገራችን ደመኛ ጠላት የሆኑ፤ ቅጥረኛና ተላላኪ በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው፡፡ እናም የሌለ ታሪክ ፈጥረው ወዳጃቸው ሻዕቢያ ሊወረር እንደሚችል በማስመሰል ቢያላዝኑ አይገርምም፡፡

ታዲያ ከሃዲዎቹ ስለ ወረራ በቂ ግንዛቤ የለንም የሚሉ ከሆነ፤ የመንን፣ኢትዮጵያንና ጅቡቲን በወረራ ካዳረሱትና በሥራው ልምድ ካካበቱት ከጡት አባታቸው በቂ ትምህርት መውሰድ ይችላሉ፡፡

ከዚህ ውጪ የኢትዮጵያ መንግሥትና የግብፅ ልዑክ በወቅቱ በጋራ ሀገራዊ ጥቅም ዙሪያ የተወያዩትን ጉዳይ አንዳንድ "ተቃዋሚ ነን" ባዮች ከእንቅልፋቸው በተነሱ ቁጥር በሚያልሙት ቅዥት በየቀኑ በጥላቻ መዝገበ ቃላት እየተተረጎመልን ማንበብ አንገደድም፡፡

ቀደም ሲል በሀገራችን ሕዝብ ላይ መጥፎ ዕይታ የነበራቸው ግብፆች የሠላምን በር ለማንኳኳት በወቅቱ መምጣታቸው መንግሥትና ሕዝቡ በተከተሉት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አማካይነት በዲፕሎማሲው ረገድ የተጎናፀፉትን ታላቅ ድል የሚያመላክት ነው፡፡

በዚህ ድል ዓይናቸው ደም ለብሶ የሚቀኑ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ግን በል ሲላቸው አጀንዳችንን ተነጠቅን፣ ሲያሻቸው ደግሞ ገንዘብ አታዋጡ፣ ቆየት ብለውም የአገር ጥቅም

አልተጠበቀም የሚሉ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ በጥላቻ የታፈኑ የፈጠራ ወሬዎችን በየሚዲያው ለፍፈዋል፤

የሀገራችን ሕዝብ በሀገራዊ ስሜት ተነሳስቶ ለግድቡ ግንባታ የሚያደርገውን ሁለንተናዊ ንቅናቄ ከቶም ሊገቱት አይችሉም፡፡ በክፉ እንዳለሟት ይቀሯታል እንጂ ሀገራችን በራሷ አቅም ዓባይን ለልማት የማዋሏ ዕቅድ ተግባራዊነት ወደ ኋላ አይቀለበስም፣ እውን የመሆኑ ስኬታማ ጉዞው አይቀሬ ነው፡፡ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በሕዝቦች ጥረት ቀጥሏል፤ መልካሙ ወሬም ይኸው ነው፡፡ በቀጣይም የህዳሴውን ግድብ ግንባታ ሌላ ገጽታ እንዳስሳለን፡፡